ለአቶ መርስዔ ኪዳን

mersea.kidan@gmail.com

ሚኒያፖሊስ፣ ሜኔሶታ

ሀገረ አሜሪካ፣

ጉዳዩ፤ "የኢዴፓ የመቀሌ ጉዞ" በሚል ርዕስ ያቀረቡትን ጽሑፍ ይመለከታል፣

በቅድሚያ የከበረ ሰላምታ አቀርባለሁ። "aigaforum.com" በተባለ ዌብሳይት ላይ "የኢዴፓ የመቀሌ ጉዞ" በሚል ርዕስ ያቀረቡትን ጽሑፍ አንብቤዋለሁ። ይህንኑ ጽሑፍ በኢዴፓ የኢሜይል አድራሻ በኩል ልከውትም ደርሶናል።

የፓርቲው የውጭ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሊቀ መንበር እንደመሆኔ፣ ለላኩልን መልዕክት በወቅቱ መልስ ሳልጽፍልዎ የዘየሁት፣ ፓርቲው በባህር ዳር ከተማ ላካሄደው ሕዝባዊ ስብሰባ ዝግጅት እያደረግን ስለነበር ባጋጠመኝ የጊዜ መጣበብ ምክንያት መሆኑን በቅድሚያ ለመግለጽ እወዳለሁ። ጽሁፉ ግን በፓርቲው ኦፊሻል ዌብሳይት ላይ ወዲያውኑ እንዲወጣ ተደርጓል።

ከሁሉ አስቀድሜ ጊዜ ወስደው በኢዴፓ ያለፈና የወደፊት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ዙሪያ ያለዎትን አስተያየት በመጻፍዎ ያለኝን አክብሮት በራሴና በኢዴፓ የውጭ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ስም ለመግለጽ እወዳለሁ።

በእርስዎ እይታ የኢዴፓ እና የትግራይ ህዝብ የጋራ አጀንዳዎች ይሆናሉ ብለው ያቀረቧቸው "የኢትዮጵያ አንድነት፣ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት እና የትግራይ ተወላጆች ከትግራይ ውጪ ያላቸው የኑሮ ሁኔታ" የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን ከጽሁፍዎ ተረድተናል። በኛ እይታ ደግሞ ከነዚህም በላይ፤ ኢዴፓና የትግራይ ህዝብ (እንደ ሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ) በሀገራዊ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ አጠቃላይ አጀንዳዎች እንዳሏቸውና ከሁሉም በላይ ደግሞ በሰብአዊ መብት፣ በመልካም አስተዳደር፣ በመሰረተ ልማት፣ በኑሮ ውድነት፣ በመሬት ባለቤትነት፣ በፀጥታና ፋይሉ ባልተዘጋው የድንበር ጉዳይ፣ በባህር በርና በሌሎችም የዴሞክራሲ ጥያቄዎች ዙሪያ የጋራ አጀንዳዎች አሏቸው ብለን እናምናለን። ስለሆነም፤ ኢዴፓና የትግራይ ህዝብ አሁንም ሆነ ወደፊት በነዚህና በሌሎችም አገራዊ አጀንዳዎች ዙሪያ አቅም በፈቀደ መጠን ይመክራሉ፣ ይወያያሉ።

ወደ ትግራይ የምናደርገው ጉዞ ህዝቡ ኢዴፓ የሚለውን ብቻ ሰምቶ እንዲያሞግሰውና እንዲያወድሰው ሳይሆን፤ የህዝቡን ስሜት፣ ምኞት፣ ፍላጎት፣ ችግርና ቅሬታም ለማዳመጥ ትልቅ ዕድል ይሰጠናል ብለን ስለምናምን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ወደፊት ለምናነሳቸው የህዝብ አጀንዳዎች ስንቅ እንደሚሆነን ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

በመጨረሻም፤ አቶ መርስዔ ኪዳን ያቀረቡልንን ከቅንነትና ከበጎ መንፈስ የመነጨ ገንቢ አስተያየትና "ኢዴፓ ወደ መቀሌ ሲሄድ እንዲህ እንዲህ ቢያደርግ" ብለው የጠቀሷቸውን ነጥቦች በተመለከተ፤ ኢዴፓ የተነሳለትን ህዝባዊ ዓላማ ከግቡ ለማድረስ በሚያደርገው ቀጣይ እንቅስቃሴ ከግንዛቤ እንደሚያስገባቸውና በግብዓትነት (Input) እንደሚጠቀምባቸው ከወዲሁ ላረጋግጥልዎ እወዳለሁ፡፡ የእርስዎም ገንቢ አስተያየት እንዳይለየን አደራ እላለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

አብዱራህማን አህመዲን
የኢዴፓ የውጭ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ሊቀ መንበር